## ሕግና ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡፡ [1]

### ከጆ. ክሪቺናቢች ፡፡

### የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡፡

### መ ግ ቢ ያ ፡፡

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ከቀሩት ፡ ከሰሐራ ፡ በስተደቡብ ፡ ከሚገኙት ፡ አፍሪቃውያን ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ አኳኋን ፡ በጣም ፡ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነትን ፡ ያሳያል ፡፡ ኢትዮጵያ ፡ ተለይታ ፡ የራሷ ፡ የሆነ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕግ ፡ ነበራት ፤ አሁንም ፡ ከጥንታዊ ፡ ባህሏ ፡ ከልማድ ፡ ሕግ ፡ (ከኮመን ፡ ሎው) ፡ እና ፡ ከአህጉራዊው ፡ ኤውሮጳ ፡ ሕግ ፡ ፅንሰ -ሐሳብ ፡ የተዛመደ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ ችላለች ፡፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕግና ፡ (ፕራይቬት ፡ ሎው) ፡ የጋራ (የሕዝብ) - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ (ፕብሊክ ፡ ሎው) ፡ የሚደረገው ፡ የእድገት ፡ እርምጃ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልነበረ ፡ አዲስ ፡ ነው ፡፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፖለቲካ ፡ አቋሞች ፡ ጥንታዊውን ፡ የአገዛዝ ፡ ፅንሰ - ሐሳብ ፡ [2] ሳይለቁ ፡ ቀስ ፡ በቀስና ፡ በጥንቃቄ ፡ ያደረጉትን ፡ መሻሻል ፡ ስንመለከት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከቀሩት ፡ አፍሪቃውያን ፡ አገሮች ፡ የተለየች ፡ መሆኗን ፡እንገነዘባለን ፤ በግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ ልክ ፡ የዚሀ ፡ ሁናቴ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ፡፡ ዳግም ፡ ከሌሎቹ ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ በመለየት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ በግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ መሻሻል ፡ ጠቅላላና ፡ ድንገተኛ ነው ፡፡ የኢትዮጵይ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መሻሻል ፡ በዚች ፡ ብጥብጥ በተጻረራት ፡ የአፍሪቃ ፡ አህጉር፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሰላምና ፡ የፖለቲካ ፡ መረጋጋት ፡ ያለባት ፡ አገር ፡ የማድረግን ፡ ውጤት ፡ አስገኝቷል ፡፡ የግል - መብት ፡ ነክ ፡ ሕጋችንም ፡ የከመ ፡ ቅጽበት ፡ መሻሻል ፡ ምክንያቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ተብራርተዋል ፡፡

በአንድ ፡ በኩል ፡ የመሬት ፡ ይዞታን ፡ የቤተ፡ ዘመድ ፡ ሕግን ፡ እና ፡ ውርስን ፡ የሚመለከት ፡ የጐሣ ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ እና ፡ በአንድ ፡ አካባቢ ፡ የተወሰነ ፡ መልክ ፡ ስላለው ፤ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ውልን ፡ የመሰለ ጉዳይን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ ጨርሰው ፡ አለመኖር ፡ ንግድን ፡ ገንዘብን ፡ በጥ

1. የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቍ ፩ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም.) ፡ ገጽ ፡ ፶፭ ፡ ላይ ፡ ከጆርጅ ፡ ክሪቺናቢች ፡ ተጽርሶ ፡ የወጣው ፡ "ኢኔው ፡ ሌጅዝሌቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ካስተመሪ ፡ ሎው" ፡ (የሕጉን ፡ ወደ ፡ ልማድ ፡ አዲስ ፡ አቀራረብ) ፡ የሚለው ፡ ነው ፡፡ የዚህ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ጨርሶ ፡ አልቋል ፤ በሱም ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ ድርሰት ፡ በሕግ ፡ መጽሔት፡ ወይም፡ በማርኛ፡ ቋንቋ፡ ታትሞ ፡ ከዚህ፡ በፊት፡ አልወጣም ፡፡

2. ከጆርጅ ፡ ክሪችናቢች ፡ "ዘሬዥም ፡ ኦቭ ፡ አሲምብሊ ፡ ኢን፡ ኢትዮፒያ" (ለኢትዮጵያ ፡ የምክር ፡ ቤቶች ፡ ሸንጎ ፡ አዘረጋግ) ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቍ ፩ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም.) ገጽ ፡ ፻፱ ፡ ላይ ፡ ከወጣው ፡ ጋር ፡ አነጻጽር ፡፡

ቅም ፡ ላይ ፡ ማዋልንና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ መሻሻልን ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ [3] እንደ ፡ ጨፆኑት ፡ የታመነ ፡ ነው ። የአፍሪቃን ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ወደ ፡ ተፈላጊው ፡ ዘመናዊነት ፡ ለማራመድ ፡ ሥራው ፡ ተጀም ሯል ፤ ካልተጀመረም ፡ የመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ አልፏል ። ባህል ፡ በተሰፋፉባቸ ውና ፡ ጠንካራ ፡ በሆኑባቸው ፡ ከላይ ፡ እንደጠቀስናቸው ፡ ዐይነት ፡ የሕግ ፡ ክፍ ሎች ፡ ተፈላጊ ፡ ዘመናዊነትን፡ ለማድረግ ፡ በጣም፡ ያዳግታል ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፤ በምን ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ የግል - መብት ፡ ነክ፡ ሕግ፡ ሊሻሻል ፡ ይችላል ? ላለው ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማሻሻል ፡ (ኢቮሉሽን) ፡ ወይስ ፡ በጠቅላላው ፡ ገለባብጦ ፡ መለወጥ ፡ (ሪቮሊሽን) ፡ ይበጅ ፡ ይሆን ?

የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ረቂቅን ፡ ያወጣው ፡ ሊቅ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አር. ዴቪድ ፡ "በጠቅላላ ፡ ገለባብጦ ፡ መለወጥ ፡ (ሪቮሊሽናሪ) ፡" ይሻላል ፡ የሚ ለውን ፡ ሐሳብ ፡ ተከትሏል ። አስተያየቱንም ፡ እንደሚከተለው ፡ ገልጾአል ፡—

የኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደፊት ፡ መራመድና ፡ ዘመናዊ ፡ መሆን ፡ በሌ ላው ፡ አገር ፡ የሚሠራበትን ፡ ሕግ ፡ መውሰድ ፡ አስፈላጊ ፡ አደረገው ። ---- ይህም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተፈላጊውን ፡ ዝቅተኛ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የተረጋ ገጠ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ---

እኛ ፡ ( አውሮጳውያን ) ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕጋችን ፡ የማይለዋወጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ እንላለን ። ዳግም ፡ በልማድ ፡ ከሚሠሩባቸው ፡ ሌላ ፡ አዳ ዲስ ፡ ሕጎችን ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ በጣም ፡ ያስቸግረናል ። --- ሆኖም ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ አስተያየት ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለ፡ አይደለም ። --- ጥቂቶችን፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጡትንና ፡ አሁ ንም ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ልማዶች ፡ እንደያዘች ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕጎቿን ፡ አቋም ፤ የሕዝቧ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ድረስ ፡ ቢለወጥ ፡ እንኳ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ትሻለች ። ስለ ዚህም ፡ ኢትዮጵያውያን፡ አዲሱ፡ የፍትሐ፡ ብሐር ፡ ሕግ፡ የጥንት ፡ ልማዶችን ፡ ለማጠቃለል ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አይገምቱም ። የሕዝቡ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በጠቅላላው ፡ እንዲለወጥ፡ የታሰበ፡ ሥንጠረዥ ፡ እንዲሆን ፡ ስለሚመኙ ፤ በይበልጥ ፡ ሕጉ፡ ወደፊት ፡ እንዲፈጠር ፡ ለታሰበው፡ የማኅበራዊ፡ ኑሮ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ አዲስ ፡ ደንቦች ፡ እንዲያዝ ፡ ይጠይቃሉ ። ( የተቀሩትን ፡ ክርክሮች ፡ ከዚህ ፡ አልጠቀስናቸውም ። ) [4]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸውን ፡ አስተያየት ፡ የአሁኑ ፡ ደራሲ ፡ ይደግፈዋል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የባህላዊ ፡ ደንቦች ፡ ለአንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ (ለምሳሌ ፡ ውል) ፡ በፍጹም ፡ አለመኖርና ፡ በሌላም ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ (ለምሳሌ ፡ የቤተ ፡

በላለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት፡ ለምሳሌ ፡ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ መጽሔትንና ፡ የሪሰይ ፡ ፔናን ፡ ተመል ክት ።

ክሪኔ ፡ ዴቢድ ፡ "ኤ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ ፎር ፡ ኢትዮፒያ" ፡ ( ፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ) ቱለይን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ (የቱሉየን ፡ ሕግ፡ መጽሔት) ቦልዩም፡ ፴፯ ፤ ( እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ( ከገጽ ፡ ፫፻፹—፫፻፬ ፡ እና ፡ ፲፫፫ ፡

ዘመድ ፡ ሕግ) ፡ የአብዛኞቹ ፡ የባህል ፡ ደንቦች ፡ አጠራጣሪ ፡ ወይም ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ከጐሣ ፡ ጐሣና ፡ ከጊዜ ፡ ጊዜ ፡ የተለያዩ ፡ መሆን ፡ የባህል ፡ ደንቦችን ፡ በሞላ አጠቃሎ ፡ ብቻ ፡ በሕግ ፡ ለማውጣት ፡ ይቅርና ፡ ጉዳዩን ፡ ለማጥናት ፡ እንኳ ፡ የማይሞከር ፡ አደረገው ። ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ እንዲያው ፡ በቀላሉ ፡ "ተገኝቶ" መጽደቅ ፡ አይችልም ፡ ነበር ፡ ከአገር ፡ ውስጥና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መነሻ ፡ ነቅሶ ፡ በአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ አመራረጥ ፡ መደንገግ ፡ ነበረበት ። ለዚህች ፡ አገር ፡ አንድ ዐይነት ፡ መልክ ፡ --- የሆነ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ የሚቻል ፡ የነበረው ፡ በውቀው ፡ በሚያደርጉት ፡ የማሻሻል ፡ ሙከራ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሰጡት ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የመጀመሪያው ፡ ነገር ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ የማኅበራዊ ፡ አኗኗር ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለማራመድ" ፡ ነበር ። ሕግ ፡ የሚገኘው ፡ ባልታሰበና ፡ ሊታወቅ ፡ በማይችል ፡ መንገድ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከባህል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ዶጋማው ፡ የሚያስተምሩ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮንና ፡ ታሪክን ፡ በሚመለከት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ሳይንስ ፡ ተከታዮች ፡ እምነት ፡ ዕውነት ፡ የሚመስለው ፡ ----እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በማወዳደር ፡ ጽኑ ፡ አካባቢ ፡ ባለበት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸ ፡ እምነት ፡ (ትምህርት) ፡ ጥንታዊ ፡ ባህል ፡ ላላቸው ፡ የውጭው ፡ ዓለም ፡ ያመጣው ፡ የሥልጣኔ ፡ ውድድር ፡ በድንገት ፡ የገጠማቸው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላሉ ፡ አገሮች ፡ አምበዛም ፡ አይስማም ። እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጎችን ፡ ያቀረበው ፡ ዓላማ ፡ የሚሠራበትን ፡ ልማድ ፡ ለማስከበር ፡ ሳይሆን ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ መነሻ ፡ መደብ ፡ ለመፍጠር ፡ ነው ። (ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ለመረዳት ፡ እንደሚቻለው ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የማሻሻል ፡ ዓላማ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ) [5]

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ልማዶች ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ ክፍል ፡ አሁን ፡ ተቀንሷል ። ሆኖም ፡ በፍጹም ፡ አልጠፉም ፡ ስለነሱም ፡ ጥናት ፡ ቢደረግ ፡ ጥቅም ፡ ሳይሰጥ ፡ አይቀርም ። በዚህች ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተንት

5. ከጆርጅ ፡ ክሽቼኖቪች ፡ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ ኢትስ ፡ ዩዝፉልነስ ፡ ሪሌሽን ፡ ቱ ፡ ከስተም ፡ ኤንድ ፡ አፕሊከቢሊቲ" ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጥቅሙ ፡ ከአገር ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ዝምድናና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ) ፡ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፪ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም.) ፡ ከገጽ ፡ ፻፸፪ ፻፸፬ ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የዚህ ፡ መሻሻል ፡ መሳኪት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርትና ፡ ከፍትሕ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ ለሰሙ ፡ ብቻ ፡ የመቀበል ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣው ፡ (ባህላዊ) ፡ አስተያየት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። (ይህም ፡ በቀረው ፡ በአፍሪካ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ከሚገኙት ፡ ክፉውን ፡ ከበጎው ፡ ሳይለዩ ፡ የጥንታዊ ፡ አባቶችን ፡ ልማድ ፡ በኩለንተናው ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ ከመቀበል ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ በማነጻጸር ፡ ነው ። ) በኢትዮጵያ ፡ ማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ ወግ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የምርምር ፡ ፍላጎት ፡ ይኸንን ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መትጋት ፡ ሳይለውጠው ፡ የቀረ ፡ ይመስላል ።

ነን ፡ በማጥናት ፤ ልማድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የያዘውን ፡ቦታ ፡ እና ያለን ። እንዲሁም ፤ ልማድን ፡ የሚሽረውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፤ ስለ ሱም ፡ የተሰጡትን ፡ መግለጫዎች ፡ በተጨሪ ፡ ልማድን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እን ዲውል ፡ የሚያስችሉትን ፡ አምስቱን ፡ መንገዶች ፡ ተራ ፡ በተራ፡ እናብራራለን ። በመጨረሻም ፡ መደምደሚያ ፡ ይሰጣል ።

ልማድን ፡ የሚሽረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ።

የሎንዶን ፡ ስብሰባ ፡ ስለ ፡ "ፊዊቸር፡ ኦቭ፡ ሎው ፡ ኢን ፡ አፍሪካ" ፡ (የሕግ ፡ የወደፊት ፡ ሁናቴ ፡ በአፍሪቃ፡ ውስጥ) ፡ (እ. ኤ. አ. ጥር ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በሚል ፡ አርዕስት ፡ ካደረጋቸው ፡ ክርክሮች ፡ አንደኛው ፡ ሕግ ፡ አውጪዎችና ፡ ዳኞች ፡ ልማድን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ከጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ማስማማት ፡ እንደሚ ችሉ ፡ ነው ። [6] በዚህ ፡ ስብሰባ ፡ በይፋ ፡ የጸደቀው ፡ የቀስ፡ በቀስ ፡ ማለማመድ ፡ ዘዴ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሉንዶኑ ፡ ስብሰባ ፡ በተደረገበት ፡ ዓመት ፡ የወጣው ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ልማድን ፡ አብዛኛውን ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ከሚሽረው ፡ ከኢትዮጵያው ፡ አቀራረብ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፤

<u>የተሻሩት ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች ።</u>

<u>ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ፡ ከሌለ ፡ በቀር፡ በዚህ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈውይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ በስተተካ ፡ ተሽረዋል ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ተቃራኒ ፡ ወይም ፡ ያለፉ ፡ ሕጎች ፡ ቢሆኑም ፡ የቀድሞ ፡ ሕግና ፡ ልማዶችን ፡ ሁሉ ፡ ይሽራቸ ዋል ። በፍትሐ ፡ ብሐር፡ ሕግ ፡ ቍ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ ውስጥ፡ "በዚህ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች" ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ "ከዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን" ፡ በሚል ፡ መተካት ፡ የባህልንና ፡ የልማ ድን ፡ መውደም ፡ ያሳንሰው ፡ ነበር ። ይህ ፡ አነጋገር ፡ የመሻሪያው ፡ ሕጉ፡ ሕግን ፡ የማያሟሉትን ፡ ልማዶች ፡ ሳይነካ ፤ በሚቃወሙት ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይወ ሰነው ፡ ነበር ። [7] በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ይህ፡ ያለፈን፡ ሕግ ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ አጥ ፍቶ ፡ መሻር ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደርጎ ፡ የማይታወቅ ፡ ነው ። ይልቁኑ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ሕግ ፤ ቬንቶዝ ፡ ፴ ፤ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፤ የሚመሳሰል ፡ ነው ።

6. ኤ. ኤን. አሎት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያወጣውን ፡ "ዘ ፡ ፊውቸር፡ ኦብ ፡ ሎው ፡ ኢን ፡ አፍሪካ" ፡ (የሕግ ፡ የወደፊት ፡ ሁናቴ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ) ፡ ሎንዶን ፤ በተርወርዝ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፩ ፡)ዓ. ም. የታ ተመውን ፡ ተመልከት ።

7. አርግጥ ፡ ነው ፡ ተፈልጎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጠቅላላ ፡ ሻሪ ፡ አንቀጽ ፡ ሳያወጣ ፡ ይህንኑ ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ በተቻለ ፡ ነበር ።
እንደዚሁ ፡ (ዐይነቱ ፡ ዘዴ ፡ «ባልተገለጸ ፡ አኳኋን» ፡ የተሻሩ ፡ ሕጎችን ፡ የመቀበል ፡ ልማድ ፡ ለሌላው ፡ ኅብረ ፡ ሰብ ፡ እምብዛም ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ።)

ኤም. ፕላኒዮል ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ ትሪታይዝ ፡ (ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያዘጋጀው) ፡ መጽሐፉ ፡ [8] ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጥቷል ፤ "ያ ፡ ድንጋጌ ፡ (ሕጉ) ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግን ፡ ሲያውጅ ፡ ማንኛውንም ፡ የቀድሞ ፡ ሕግ ፡ ሻረ ። — እንደዚህ ፡ ካለው ፡ ታላቅ ፡ አደራረግ ፡ ጋር ፡ የሚነፃጸር ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ አንድም ፡ አልነበረ — ።" ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ እየተሻሻለ ፡ የመጣውን ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ለመጨረሻ ፡ ሲያጠናቅቅ ፤ የኢትዮጵያው ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ያልተለመደ ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፅንሰ ሐሳብ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ አስመጣ ። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ውጤት ፡ "ሕዝቡ ፡ እንዳይሠራም ፡ ቢደነገግ ፡ የተከለከለውን ፡ ተግባር ፡ ስለ ማይተው ፡ ጥቅመቢስ" ፡ [9] ያደርገዋል ፡ ተብሎ ፡ መጠበቁ ፡ አይቀርም ። በዚህም ፡ ሁናቴ ፡ አንዳንድ ፡ ሕጎችን ፡ ሳይለዩና ፡ ሳይመርጡ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ ያዘዘው ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበር ፡ መጐትጐት ፡ የሕዝቡን ፡ በጸጥታ ፡ መኖር ፡ ያዳከመዋል ። አለመግባባቶችም ፡ ሕግ ፡ ሳይጠቅስና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይኬድ ፡ መፍትሔ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ። ከዚህ ፡ ጽሁፍ ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የግድ ፡ መሆን ፡ እንደሌለባቸውና ፡ አኳኋናቸውም ፡ በመደዳው ፡ እንዳልሆነ ፡ ለማሳየት ፡ ነው ። በዕውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ በጠቅላላ ፡ ልማድን ፡ በመሻርና ፡ ሁሉንም ፡ ጉዳይ ፡ አቅፎ ፡ በመያዝ ፡ ሁኔታ ፡ የተሠራ ፡ ሕጉግ ፡ በማውጣት ፡ የወሰደችውን ፡ እርምጃ ፡ የሚደግፉና ፡ የሚያስረዱ ፡ (፩ኛ)ባህላዊ ፡ (፪ኛ) ፡ አሁን ፡ የሚሠራባቸውና ፡ (፫) ፡ የቅልጥፍና ፡ (ስሙም ፡ የመሆን) ፡ ምክንያቶች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ ማስረጃዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይብራራሉ ።

## ባሕላዊ ፡ ምክንያቶች ።

ኢትዮጵያ ፡ በባህል ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ አፍሪቃዊ ፡ ነች ፡ ተብላ ፡ አትገመትም ። ባህሏም ፡ የመካከለኛው ፡ ባሕር ፡ (ሜዲትራኒያን) ፡ ሥልጣኔ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ (በስሕተት ፡ "የምዕራብ" ፡ ሥልጣኔ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው) ፡ ጠባዮችን ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፤ የአይሁድ ፤ የክርስቲያን ፤ የግሪክና ፡ የሮማን ፡ ሥልጣኔ ፡ ጠባዮችን ፡ ይጨምራል ። ቆንስጣንጢኖስና ፡ የኒቂያው ፡ ጉባኤ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ፤ የአክሱሙም ፡ መንግሥት ፡ ከንጉሥ ፡ ጀስቲኒያን ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ። ከማንኛውም ፡ ይልቅ ፡ ይህችን ፡ አገር ፡ በመከራና ፡ በፈተና ፡ ጊዜ ፡ ከመከፋፈል ፡ ያዳናት ፡ አንድ ፡ ማእከላዊ ፡

8. ኤም ፡ ፕላንዮልና ፡ ጂ ሪፒፒርት ፡ ትሪቲዝ ፡ ኦን ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ (በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያዘጋጀው ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ (፲፪ኛው ፡ እትም ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፴፱) ፡ በሉዊዝና ፡ ግዛት ፡ ሕግ ፡ ኢንስቲቱት ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. የተተረጐመው ፡ ሾልዩም ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ቁ. ፪፻፩፮ ።

9. አሎት ፡ እላይ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ የጠቀስነው ፡ ፮ኛ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፤ ገጽ ፡ ፴፫ ፡ ላይ ።

የሆነ ፡ ሕግና ፡ ሥልጣን ፡ በባህላዊ ፡ ውስጥ ፡ የቆየ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሕግን ፡ በሰፊው ፡ ማገግ ፡ በኢትዮጵ ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ወደ ፡ ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ገደማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሚተዳደሩበት ፡ ጥንታዊ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕግና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተጠቃለሎ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ (የነገሥታት ፡ ሕግ) ፡ ወጣ ። የዚህም ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ ዋና ፡ ሐሳቦች ፡ የተወሰዱት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እናት ፡ ከነበረችው ፡ ከእስክንድሪያ ፡ የተዋሀዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበር ፡ በተጨማሪም፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ከምሥራቃዊ ፡ የሮማ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ሐሳቦችን ፡ ወስዶአል ። ስለ ዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በይበልጥ ፡ ለማወቅ ፡ የሚሹ ፡ አንባቢዎች ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም. ሚላኖ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ አር. አር. ካንቫረ ፡ በተረጐመው ፡ "ፍትሐ ፡ ነገሥት" ፡ በሚለው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችላሉ ።[10]

ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ወደ፡ አለው ፡ ሁኔታ ፡ ተመልሰን ፡ ብንመለከት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሕግ ፡ ማገግ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ቢሆንም ፡ ገና ናው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ዘመኑ ፡ ያለፈበት ፡ በመሆኑ ፡ እምብዛም ፡ አይጠቀስም ። እ. ኤ. አ. ከ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገሮች ፡ የሚዳኙት ፡ በልማድና ፡ በርትዕ፡ ( ኢኩቲ ) ፡ (አግባቢ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርዶችም ፡ ጭምር ፡ )መሠረት፡ ሳለ ፡ ልማድም፡ የተለያየና፡ አጠራጣሪ ፡ ነበር ። ከኤርትራ[11] ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በስተቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ ተደርድሮ ፡ አያውቅም ። ሆኖም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልማዶች ፡ በኅብኛዎች ፡ መጽሔትና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ጥናት ፡ (ኤትኒኦሎጂ) ፡ መጽሔት ፡ በሰፊው ፡ ተገልጸው ፡ ይገኛሉ ።[12] የየጎሳውና ፡ የየአገሩ ፡ የልማድ ፡ ሕግ የተለያየ ፡ ዐይነት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መንደላቀቅ ፡ በቀረበት ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጓጓትና ፡ መሻሻል፡ በጣም ፡ የተፋጠነ ፡ ዘዴ ፡ የሚያሻው ፡ ሲሆን ፡ እነዚህን ፡ ልማዶች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አሻሽሎ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አጠቃሎ ፡ ማገግ ፡ የብዙ ፡ ትውልድ ፡ ዕድሜ ፡ የሚጠይቅ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ትክክለኛም ፡ ሆነ ፡ ስህተተኛ ፡ ያለፈውን ፡ ሕግ ፡ ጠራርጐ ፡ የሚሽር ፡ የዛሬውን ፡ የኢትዮጵያ ፡

10. አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ጻድዋ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ፡ ከነብራሪያውና፡ ማስረጃው ፡ ጭምር ፡ የተረጐሙት ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽሐፍ ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ታትሞ ፡ ይወጣል ።

11. ኤፍ. ኤፍ. ረሰል ፡ "ኤርትርያን ፡ ከስተማሪ ፡ ሎው" ፡ ( የኤርትሪያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ) ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፳ልዩም ፡ ፫ ፡ (እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ.ም. ) ገጽ ፡ ፶፱ ፡ ተመልከት ። በዚህ ፡ ጥናት፡ የታወቀው ፡ ጽሑፍ ፡ በኢ.ና. አእስቲኒ ፡ የተጻፈው ፡ ትራታቶ ፡ ዲ. ዲሪቶ ፡ ኮንሱቱዲናሪዮ ፡ ዴል ፡ ኤሪቲሪያ ፡ ( አሥመራ ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፮ ) ።

12. በተጨማሪም ፡ ለምሳሌ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦብዘርቨርና ፡ ባላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በጻፉአቸው ፡ የአማርኛ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ተመልከት ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ በማገግ ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ተወስዶል ። ቢሆንም ፡ ይኸ ፡ ያልተለመደ ፡ ዘዴ ፡ ባለፈው ፡ ፩ ባሁኑና ፡ በወደፊቱ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ የተያያዘ ፡ አረማመድ ፡ የተጠበቀ ፡ እንዲሆን ፡ ጥሩ ፡ ብልሃቶችን፡ ጨምሮ ፡ ይዞአል ። ይኸ ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይብራራል ። የአህጉራዊ፡ አውሮጳውያንን ፡ መስመር ፡ በመከተል ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግን ፡ ረቂቅ ፡ ያዘጋጀው ፡ የታወቀው ፡ ሊቅ ፡[13] የራሱን ፡ አስተያየት ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ለመጨመር ፡ ፈቃደኛ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ለክርክራችን ፡ መነሻ ፡ እንዲሆን ፡ በፍትሐ ፡ ብሐር ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠውን ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መጥቀስ ፡ ሳይረዳን ፡ አይቀርም ።

> "በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከጥንት ፡ ዘመናት ፡ ከወረስናቸው ፡ በጽኑ ፡ ከተመሠረቱት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ የሕግ ፡ ልምዶች ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡ ናቸው ። - - - እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ ተሽለው ፡ የሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ ተጠንተዋል ። ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ የሰዎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ለማግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከወጣላቸው፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ፡ ፍላጎታቸውን፤ ልምዳቸውን ፡ ወይም፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም" ።

ይህ ፡ ብልህና ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ አነጋገር ፡ ያለምርማሪ ፡ እንዳለ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሲነበብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደገና ፡ ከተጠቀሰው ፡ ልማድን ፡ ከሚሽረው ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።

> "ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ በዚህ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ። "

ነገር ፡ ግን ፡ ጠለቅ ፡ ብለን፡ የተመራመርን፡ እንደሁ ፡ ሲወርዱ ፡ ሲዋረዱ ፡ የመጡት ፡ ባሕላዊ ፡ ደንቦችና፡ ልማዶች፡ የተጠበቁባቸውና ፡ ሊጠበቁ ፡ የሚቻልባቸው ፡ አምስት ፡ ዘዴዎች ፡ መኖራቸውን ፡ እንገነዘባለን ። እነዚሁም ፤ (፩ኛ) ፡

13. ስሙ ፡ ጥሩ ፡ የሆነው ፡ የፓሪስ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲው ፡ ምሁር ፡ በተመዘዘኝ ፡ ጥናት ፡ የታወቀው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዳቪድ ።

ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት [14] (፪ኛ) ፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ (መጥቀስ) ፤ ፫ኛ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መድፈን ፡ (መሙላት) ፤ (፬ኛ) ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤና ፡ (፭ኛ)፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንገልጻቸዋለን ።

## የልማድ ፡ መጠቀሚያዎች ።

### (፩ኛ) ፡ ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ።

አብዛኛው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ውስጥ፡ ፡ ተጨምሮ ፡ ከመሻር ፡ ድንዋል ። በዚሀ ፡ አኳኋን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቅርጽ ፡ አግኝተው፡ የገቡት፡ ልማዶች ፡ በጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ይሆናሉ ። እንደዚሀ ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ የራሱ ፡ ፍጥረት ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይ ሠራበት ፡ ያግደዋል ። ይኸም ፡ ባይሆን ፡ አጋጊው ፡ በጠቅላላ ፡ ልማድ ፡ ላይ ፡ እን ኳን ፡ የነበረው ፡ አቀራረብ ፡ አንዱን ፡ ከአንዱ፡ በመምረጥ ፡ የተመሠረተ ፡ ነበረ ። ይህንንም ፡ ካልን ፡ ዘንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አጋጊ ፡ ለአመራረጡ ፡ የተጠቀመ ባቸውን ፡ ተገቢ ፡ የአመራረጥ ፡ መመጠኛዎች ፤ በዝርዝር ፡ ሳይሆን ፡ በአጭሩ ፤ ከዚሀ ፡ ላይ ፡ እናቀርባለን ። እዚሀ ፡ ላይ ፡ ምርጫው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ ምክንያቱም ፡ "የተሻሩት ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች" ፡ በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ሥር ፡ ያልተጨመረ ፡ ሁሉ ፡ እንደተተወና ፡ እንደተሻረ ፡ ስለሚታወቅ ነው ።

ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሲዘጋጅና ፡ ሲታገግ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንና ፡ ፓርላማ ፡ ያደረጉት ፡ ክርክርና ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ተጽፎ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በግልጽ ፡ አልወጣም ። ቢሆንም ፤ ከአሉባልታ ፡ ሳይሆን ፡ ከመጨረሻው ፡ ከሕጉ ፡ ዝግጅት ፡ ውጤት ፡ እንደተረዳነው ፡ "ጠቅላላው" ፡ የአገሪቱ ፡ ልማድ ፡ (የእስዋ ፡ "የልማድ ፡ ሕግ") ፡ በሚከተሉት፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ሲገኝ ፡ ከሞላ ጐደል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጨመረ ፡ በቅድ ሚያ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ እንችላለን ። ሁኔታዎቹም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ (ሀ) ፡ አብዛኞቹ ፡ ደጋ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የያዙት ፡ ልማድ ፡ የሆነ ፡ እንደሁ ፡ ከላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ልማዱን ፡ "ጠቅላላ" ፡ (የጥንት) ፡ ሊማሰኝት ፡ በቂ ምክንያት ፡ የሆናል ፤ (ለ)ልማዱ ፡ በዚያ ፡ የመጨረሻ ፡ የበላይ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሁለንተና ፡ ውስጥ ፡ ሰርጐ ፡ የሚገኘውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕ የማይጻይፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ (ሐ) ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ የሚደረገው ፡ የወደፊት ፡ እርምጃ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ግጼታ ፡ ልማዱ ፡ የሚቃ

14. "ሕግ ፡ አርጐ ፡ ማዘጋጀት" ፡ ከማለት ፡ ሳይሻል ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም፡ የአገር ፡ ልማዶችን ፡ እንዳሉ ፡ ይዞ ፡ በመጠቀም ፡ ፈንታ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከተወሰዱት ፡ መፍትሄዎች፡ ጋር ፡ ለማመሳሰል ፡ ተሻሽለ ፡ ነው ። ወይም "የተጨቃለሉ" ፤ ይህ ፡ ቃል፡ በተጨማሪ ፡ ከጥንት ፡ ልማዶች ፡ ጥቂቶች ፡ አሁንም ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ይገልጻል ፡ ማለቱም ፡ ያስኬዳል ።

ወም ፡ መሆን ፡ የለበትም ፤ (የኋሊት ፡ የሚራመድ ፡ የመሬት ፡ ማስተላለፍ ፡ [15] ሥርዐት ፡ አሁንም ፡ እንዳለ ፡ የተተወው ፡ ለጊዜው ፡ ከመሆንም ፡ በላይ ፡ አንድ ዐይነት ፡ አቅድ ፡ ይዞ ፡ በሌላው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ያለመገኘቱ ንና ፡ እሱም ፡ የሚመለከተው ፡ የአገር ፡ ልማዶችን ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጋ ። ) (መ) ልማዱ፡ በፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ፡ ቃላት፡ ሊገለጥ፡እንደሚችል ፡ በበቂ ፡ ሁኔታ ፡ ብዩሀና ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ፡ውስጥ ፡ የገቡትም ፡ ልማዶች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከተቀበልናቸው ፡ መላዎች ፡ ጋር ፡ አብ ረው ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ዕንስ—ሐሳብ ፣ መደቦችና ፡ አከፋፈሎች ፡ አሠራር ፡ ተቀ ላጥፈው ፡ ነው ፡ የተበጁት ። [16] እንደአጋጣሚ፡ ሆኖ ፤ ከዚህ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ አራት ፡ ሁኔታዎች ፡ መቅድም ፡ ሆኖ ፡ በተሰጠው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሪ ፡ ቃልም ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። (ሀ)፡ ጥንታዊ፡ "ልምዶችን" ፤ (ለ) ፡ "የተፈ ጥሮ ፡ ፍትሕትን ፣ (ሐ) ፡ የተቀባዮችን ፡ "ፍላጎትትንና" ፤ (መ) ፡ የሕግ ፡ ግልጽነ ትን ፡ በመቅድሙ ፡ ውስጥ ፡ ተነግሮል ። [17]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ የአመራረጥ ፡ መመጠኛዎች ፡ ስለግዴታዎች ፡ የሚለውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ አራተኛ ፡ መጽሐፍና ፡ በተለይ ፡ የወጣውን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አፈላለቃቸው ፡ በጣም ፡ ባዕድ ፡ እንዲሆን ፡ አደረገው ። ይህም፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ለንዚህ ፡ ዘመናዊ፡ ለሆኑት ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች፡ ተስማሚ ፡ የሆኑ ፡ የአገሩ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ፡ ስሊታጡ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፣ ከጥንት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ለመጡት ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ በርስትና ፡ በው ርስ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ብዙ ፡ ተስማሚ ፡ የጥንት ፡ ልማዶች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደርገዋል ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ የተደረጉትን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማ ዶች ፡ (ከትውስት ፡ ሕጎች ፡ ለይቶ) ፡ መዘርዘር ፡ ከዚህ ፡ ጽሁፍ ፡ ወሰን ፡ ውጭ ፡ ይሆናል ። አብዛኛዎቹም ፤ ግላዊ ፡ ሕግን ፡ (ስለሰዎች ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው) ፡ ዘመድ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። እንዚሁም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በየቦ ታው ፡ መለያየታቸው ፡ ቀርቶ ፡ ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ይሆናሉ ። የዚህ ፡

15. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ ፻፳፫፻፮፫—፹፯ ።

16. በንገራችን ፡ ላይ ፡ ከዚሁ፡ የተነሣ ፡ በፈረንሣይኛ፡ የተጻፈውን፡ ዋና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ለዚህ ፡ ጥናት፡ ተስማሚ፡ ባለሆኑት ፤ ግን፡ መደበኛ፡ (ኦፊስል) ፡ ወይ፡ ሆኑት፡ የአማርኛና፡ (ባለሥል ጣን ፡ ነው)፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ መተርጐም ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ። አማርኛ ፡ የሕግ፡ ቃላት ፡ ያንሱታል ፡ የእንግሊዝኛ ፡ የሕግ ፡ ቃላት፡ ደግሞ፡ ለኢትዮጵያ፡ ፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ አይ ስማሙም ። ከጆርጅ ፡ ክሪቺናቢች ፡ "ኢትዮጵያን፡ ሊጋል ፡ ኢጁኬሽን" ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ትምህርት) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ምርመራ፡ መጽሔት፡ ፳ልዩም ፡ ፩ ፡ ቁ. ፩ ፡ (ኦ. ኦ. ኦ. ፲፱፻፷፫፡ ዓ. ም.) ፡ (የቋንቋ ፡ ችግር ፡ የሚለውን) ፡ ከገጽ ፡ ፷፱—፸ ፡ ተመልከት ።

17. ይኸን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ጥቅስ ፡ "--- በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ፡ የሚገኙ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ እንዲሆኑ ፡ አድርገናል ") ፤ የሚለው ፡ ነው ።

እንድ ፣ ዐይነት ፣ ሕግ ፣ ማውጣትን ፣ ብዙዎች ፣ የተቃወሙትንና ፣ በአፍሪቃም ፣ ውስጥ ፣ ከሁሉም ፣ የተለየ፣ የራሱ፣ ዐይነት ፣ ብቻ ፣ ስለሆነ ፣ ይህን ፣ ስሜት ፣ የሚቀንሱ ፣ መንገዶች ፣ በዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ውስጥ ፣ እየተደጋገሙ ፣ ይገለጻሉ ። ይህ ፣ ያለፉ ፣ ሕጎችንና ፣ ልማዶችን ፣ የሚሽር ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ የእስላሞች ፣ የግል ፣ ጉዳይ ፣ የሚወሰንበትን ፣ የቃዲዎችና ፣ የናኢባዎች ፣ ጉባኤ ቤት ፣ የተቋቋመበትን፣ ሥርዐታዊ፣ አዋጅንም ፣[18] ጭምር፣ ሽሮአልን ? የሚለው ፣ ጥያቄ ፣ በጣም ፣ ረቂቅ ፣ የሆነ ፣ የሕግ ፣ ይዞት ፣ አለው ። ይህ ፣ ጉዳይ ፣ ፖለቲካ ፣ ነክ ፣ ስለሆነ ፣ በጉዳዩ ፣ ገብቼ ፣ አሳቤን ፣ ለመስጠት ፣ ተገቢ ፣ መስሎ ፣ አይታየኝም ። በእስላሞች ፣ ግላዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ዳኝነትን ፣ የሚሰጠው ፣ የቃዲዎች ፣ ጉባኤ ፣ ሥልጣን ፣ ግን ፣ በንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ የታወቀ ፣ በመሆኑ ፣ ለጊዜው ፣ ለእስላሞች ፣ እንደሚስማማ ፣ ሆኖ ፣ የተተረጎመ ፣ ይመስላል ፤ ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ ይህንኑ ፣ የሚያብራሩ ፣ ሕጎች ፣ ይወጡ ፣ ይሆናል ።

ለምሳሌ ፣ ያህል ፣ ከዚህ ፣ ቀጥሎ ፣ በሙሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ ጠቃሚ ፣ የሆኑትን ፣ የጥንት ፣ ባህል ፣ ያስገቡ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥሮች ፣ ተሰጥተዋል ። ፲፱፻፷እና ፣ ተከታታዮቹ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ፲፱፻፷፩ ፣ ፲፱፻፷፬ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ (ያለኑዛዜ የተደረገ ፣ ውርስ ፣ ባልየውን ፣ ወይም ፣ ሚስትየዋን ፣ እንደማይጨምር ፣ ተቁጥሮ ፤) ፲፱፻፷፩ ፣ ከ፲፱፻፷—፷፱ ፣ ፲፱፻፷፯—ከ፲፱፻፲፫—፲፬ ፣ ፲፱፻፶፱ ። (፲፰) ፣ ልማድን ፣ ማመልከት ፣ (መጥቀስ) ።

አሁን ፣ በመብራራት ፣ ላይ ፣ የሚገኘው ፣ ልማድን ፣ የሚሽረው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ በመላው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ማንኛቸውንም ፣ የቀድሞ ፣ ልማድ ፣ ደንቦች ፣ "በግልጽ ፣ የሆነ ፣ ድንጋጌ ፣ ከሌለ ፣ በቀር" ፣ ይኸውም ፣ ማለት ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ከሚያመለክታቸው ፣ (ከሚጠቅሳቸው) ፣ ልማዶች ፣ በስተቀር ፣ ሌሎቹን ፣ ሁሉ፣ ሽሮአቸዋል ። የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ በውስጡ ፣ ያልተመለከተትን ፣ ወይም ፣ ያልገቡትን ፣ ሁሉ ፣ ሽሮአቸዋል ፣ የአጋጊ ፣ ሕጉንች ፣ ዕንኳንስ ፤ ልማድን ፣ ሊያሟሉና ፣ ራሳቸውም ፣ ቢሆኑ ፣ በልማድ ፣ አልተሟሉም ።[19] የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉም ፣ ፣ ልማድን ፣ የሚያያመለከ

18. የቃዲዎችና ፣ የናኢባዎች ፣ ጉባኤ ፣ ቤት ፣ የ፲፱፻፴፯ ፣ ዓ. ም. አዋጅ ፣ ፶፪ ፣ ነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ፫ኛ ፣ ዓመት ፣ ቁ. ፱ ።

19. ይህ ፣ የአገርን ፣ ባህል ፣ የማያስቀረው ፣ ሕግ ፣ ወደፊት ፣ የሚመጡ ፣ ልማዶችንም ፣ ጭምር ፣ ያስቀር ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ገና ፣ የሚታይ ፣ ጉዳይ ፣ ነው ። የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ የሚሽረው ፣ "ከዚህ ፣ --- ፣ በፊት ፣ ይሠራባቸው ፣ የነበሩትን" ፣ ብቻ ፣ ነው ። ግን ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ የሚመጡትን ፣ ልማዶች ፣ "እንዲሠራባቸው" ፣ የሚያደርግ ፣ ምን ፣ ይኖር ፣ ይሆን ? ምናልባት ፣ ዳኞች ፣ ሕጎችን ፣ በሚተረጉሙበት ፣ ጊዜ ፣ አዲሶቹ ፣ ልማዶች ፣ የመግባባት ፣ ኃይል ፤ ይኖራቸው ፣ ይሆናል ። (ከዚህ፣ በታች ፣ "ፍርዳዊ ፣ ዘይቤ" በሚለው ፣ አርእስት ፣ ሥር ፣ ከሰጠነው ፣ አስተያየት ፣ ጋር ፣ አመዛዝን) ይህ ፣ የፍራንኮ ፣ ኢትዮጵያ ፣ አቀራረብ ፣ ልማድን ፣ በመሰረዝ ፣ ፈንታ ፣ በጥቅም ፣ ላይ ፣ ከሚያውላቸው ፤ ለምሳሌ ፣ ከእስዊዝ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ጋር ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ይለያይ ፣ ይሆን ? ( የስዊስ ፣ ሕግ ፣ ቁ/፩) ።

ተው ፡ አንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ፡ ብቻ፡ ነው ። እንዚህንም ፡ ቦታዎች ፡ እዚህ ፡ ባጭሩ ፡ መግለጽ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጥ ፡ ይሆናል ። እነሱም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተገለጸው ፡ ጠቅላላ ፡ ልማዶች ፡ ሳይሆኑ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ የሚለያዩት ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ጸንቶ ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ከታየ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ይኸንኑ ፡ ከማመልከት፡ ፈንታ ፡ "በውስጡ ፡ እንደሚያስገባው ፡ " ግልጽ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩት፡ ማብራሪያዎች፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለተመለከቱት ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ናቸው ። የነዚሁም ፡ ጥቂትነት ፡ የሚያስታውሰን ፡ ሕግን ፡ ለማስተባበር ፡ የሚሞከረውን ፡ ጥረት ፡ ነው ። እንዚህንም ፡ በቤተዘመድ ፡ በውርስ ፡ በንብረት፡ በውልና ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርሱ ፡ አላፊነት ፡ በሚሉ ፡ አርዕስቶች ፡ እንገልጸቸዋለን ።

<u>ቤተዘመድ ።</u>

ቁ. ፡ ፭፻፸፯ ፡ - <u>የመተጫጨት ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርም )</u> ።

የመተጫጨት ፡ ሥርዐት ፡ መተጫጩቱ ፡ በሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቁ. ፭፻፸፰ ፡ - <u>(የመተጫጨት፡ መፈረስ፡ የሚያስከትለው ፡ ) ፪ ፡ - የሕሊና ጉዳት</u> ።

የዚህን ፡ ካሣ ፡ ልክ ፡ ለመወሰንና ፡ ካሣውን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለውን ፡ ባለመብት ፡ ዳኞች ፡ የአገሩን ፡ ልማድ ፡ መሠረት፡ አድርገው ፡ ይከተላሉ ።

ቁ. ፭፻፸፱ ፡ - <u>ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ</u> ።

(፩) ጋብቻ ፡ በአንድ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። ( እነዚህ ፡ ሹሞች ፡ በገጠር ፡ ያለመኖራቸውን ፡ አትዘንጋ ፤ የክብር ፡ መዝገቦቹ ፡ እስከሚመች ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሳይሠራባቸው ፡ እንዲቆዩ ፡ የሚያደርገውን ፡ ቁ. ፫ሺ፫፻፷፩ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ አነፃጽረው) ።
(፪) እንደዚሁም ፤ ሕጉ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ባአገር፡ ልማድ [20] ፡ መሠረት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጋብቻዎች ፡ ያውቃል ፡ ( ይቀበላል ) ።

ቁ. ፭፻፹ ፡ - <u>የልማድ ፡ ጋብቻ</u> ።

( በአንድ ፡ ጎሳ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፤ በአንድ፡ ወንድና ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ ግንኙነት ፡ የሚያስከትል ፡ የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ተፈጸመ ፡ ይባላል ። )

20. በጣም ፡ የሚያስገርመው ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አባል ፡ የሆኑት ፡ የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐታቸውን ፡ የሚፈጽሙት ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቁ. ፯፻፰ ፡ - <u>የልማድ ፡ ጋብቻ</u> ።

የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈጸም ፡ የሚቻልበት ፡ ሁኔታና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ዐይነት ፡ በአገሩ ፡ ልማድ ፡ ይወሰናል ።

ቁ. ፯፻፳፬ ፡ - ( ለልማድ ፡ ጋብቻ ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑት፡ ሁኔታዎችና ፡ ሥርዐቶች ፡ ሲጓደሉ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ቅጣትና፡ ካሣ፡ ሊወሰንባቸው ፡ ይቻላል ። )

ቁ. ፰፻፷ - ፰ ፡ ( ወላጆች ፡ ለተወላጆች፡ ወይም፡ ለጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ እንዲሁም ፡ ከአንድ ፡ አባት ፡ ከአንዲት ፡ እናት ፡ ለተወለዱ ፡ እህትና ፡ ወንድም ፡ ከአባት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ከእናት ፡ ብቻ ፡ ለተወለዱ ፡ እህትና ፡ ወንድም ፡ ሕጋዊ ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ሁኔታ ፡ የሚወሰነው ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማድ ፡ ነው ። )

<u>ማስታወሻ ።</u>

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የገቡት ፡ ጠቅላላ፡ ልማዶች ፡ በቤት፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መገኘታቸው ፡ ተገልጾ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ( ማለት ፡ የቤተዘመድ ፡ ሕግ ፡ ) የአገር ፡ ልማዶችን ፡ በጥቂቱ ፡ ማመልከቱን ፡ አየን ። ይኸም ፡ ሕጉ ፡ በአንዳንድ ፡ በተወሰኑ ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ የሚያደርሰው ፡ ውጤት ፡ በደህና ፡ እንዲቃለል ፡ መላ ፡ ይሰጠናል ። ሌሎቹም ፡ ተጨማሪ ፡ ማቃለያ ፡ ብልሃቶች ፡ ወደፊት ፡ "በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ " በሚለው ፡ አርዕስት ፡ እናቀርባቸዋለን ።

<u>ውርስ ።</u>

<u>ማስታወሻ ።</u>

የውርስ ፡ ሕግ ፡ ልማድን ፡ ጨርሶ ፡ አይመለከትም ። ስለዚህ ፤ በልማድ ፡ የሚሠሩባቸው ፡ የውርስ ፡ ሥርዐቶች ፡ ብቻቸውን ፡ ቆመው ፡ የማይጸኑ ፡ ናቸው ። ሆኖም ፤ በዕርቅና ፡ በኑዛዜ ፡ ላይ ፡ ሊጠቀሱ ፡ ሊጸኑ ፡ ይችላሉ ። ሳይናዘዝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ ሕግ ፡ "የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናት ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ " የሚለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ ( ቁ. ፰፻፴፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ ) ሊያስገባ ፡ በየቦታው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑትን ፡ የኑዛዜን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ሥርዐት ፡ ትቶታል ። የየቦታው ፡ ልማዶችም ፡ በበኩላቸው ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ሥርዐቱ ፡ ጉዳይ ፡ ሕጉን ፡ ሊተውት ፡ ይችሉ ፡ ል ። ይኸውም ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ወደፊት ፡ "በከፊል፡ ሕጋዊ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ " በሚል ፡ አርዕስት ፡ እንደምንገልጸው ፡ ሁሉ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ሽማግሌ ፡ ይዞ ፡ ዕርቅ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ንብረት ።

ቁ. ፲፻፴፪ ፡ - ("የአንድ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍሎች ፡") ፪ ፡- ትርጓሜ ።

የአንድ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍል ፡ የሚባለው ፡ በልማድ ፡ እንደሚታየው ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠረው ፡ ነው ። (ቁ. ፲፻፴፮ ፡ ይኸንን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከቱን ፡ ጉዳዮች ፡ ይሰጣል ።)

ቁ. ፲፻፷፫ ፡ - መሠረቱ ፡ (የሥሪት ፡ / የይዞታ ።)

(ለ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ሳያቋርጥ ፡ በስሙ ፡ ግብር ፡ ለከፈለ ፡ ባለይዞታ ፡ የንብረቱ ባለቤት ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ።) ስለሆነም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መሬት ፡ ሲሆንና ፡ በአገሩ ፡ ሥሪት ፡ መሠረት ፡ የመሬቱ ፡ ርስትነት ፡ የግል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ ተወላጆች ፡ የሚካፈሉት ፡ በሆነበት ፡ ሥፍራ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የትውልድ ፡ ሐረጉን ፡ መዝግቦ ፡ ርስቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይህ ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ አያግደውም ።

ቁ. ፲፪፻፷፮ ፡ - የግጠር ፡ የመተላለፍ ፡ መብትና ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ።

(የመተላለፉ ፡ መብት ፡ መጠን ፡) በቦታው ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ይሆናል ።

ቁ. ፲፬፻፹፱ ፡ - መሠረቱ ፡ (የሕብረት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች) ።

ሀብትነታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ (የደሽ ፡) እንደ ፡ የጎጣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅብረት ፡ መሠራታቸው ፡ የሕብረቱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የተከተሉ ፡ መስሎ ፡ በታዋ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚሠሩ ፡ ይሆናሉ ።

ቁ. ፲፬፻፪ ፡ - (ልማዶችን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለማድረግ ።)

ቁ. ፲፬፻፲፮ - ፲፯ ፡ (በአገር ፡ ልማድ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በልማድ ፡ የሚሠሩ ፡ ሕብረታዊ ፡ የመሬቶች ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ መኖራቸው ፡ በተጨማሪ ፡ ተገልጿዋል ።)

ማስታወሻ ።

በቁ. ፲፬፻፲፫ - ፲፱ ፡ በተሰጠው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የልማድ ፡ "ደንቦች" ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሻሻሉ ፡ እንዲቻል ፡ ሆኖአል ።

ቁ. ፲፪፻፷፫ -፷፯ ፡ (የርስት ፡ አመዘጋገብ ፡ ሕጎች [21] ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እስኪውሉ ፡ ድረስ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ለማስተላለፍ ፡ ምስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ እንዲሆኑ ፡ (ኢርጋ ፡ አምነስ ፡) መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ ሥርዐቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልማዳዊያን ፡ ደንቦች ፡ እንዳሉ ፡ እንዲቆዩ ፡ ታዞዋል ።)

21. የኢ.ት ኒያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ።

ማስታወሻ ፡፡

በአንዳንድ ፡ በመሻሻል ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የሚሠራበት ፡ በሕግ ፡ የታወጀ ፡ የምዝገባ ፡ ሥርዐት ፡ ነው ፡፡

ውሎች ፡፡

ቁ. ሺ፯፻፲፫ ፡ - ለውለታ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡፡

ውሎች ፡ አስገዳጅነታቸው ፡ በውሉ ፡ በተነገረው ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ልማድ ፡ ቅን ፡ ልቦና ፡ የውለታው ፡ ዐይነት ፡ የሚያስከትሏቸውን ፡ ነገሮች ፡ ጭምር ፡ ነው ፡፡

ማስታወሻ ፡፡

ይህ ፡ "ጸንተው ፡ ለሚገኙ ፡ ልማዶች ፡" የተሰጠው ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ የተደረገ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ሐተታ ፡ አያሻውም ፡፡ እነዚህ ፡ ልማድ ፡ የሚሠራባቸውም ፡ ጉዳዮች ፡ በተለይ ፡ የመሬትን ፡ ኪራይ ፡ በሚመለከተው ፡ የስምምነት ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ይገኛሉ ፡፡

ቁ. ፪ሺ፱፻፶፫ ፡ (፪) ፡ ፪ሺ፱፻፷፫ (፩-፪) ፡ ፪ሺ፱፻፷፯ (፪) ፡ ፫ሺ፯ (፪) ፡ ፫ሺ፲፫ (፫) ፡፡ በጥፋት ፡ ላይ ፡ ስለተመሠረተ ፡ አላፊነት ፡፡

ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ - ስለ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡፡

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የካሳውን ፡ (ለሕሊና ፡ ጉዳት ) ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ በርትዕ ፡ በአስተያየት ፡ ለመወሰንና ፡ እንዲሁም ፡ የቤተዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ለመነጋገር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ዳኞች ፡ የአገር ፡ ልማድን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ፡፡

(፪) ዳኞች ፡ እነዚህን ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ጊዜያቸው ፡ ከሕሊና ፡ ከሰብአዊ ፡ አእምሮ ፡ ተቃራኒያን ፡ መሆናቸውን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባቸውም ፡፡

ማስታወሻ ፡፡

ይህ ፡ የቦታን ፡ ( የአገሩን ፡ ) ልማድ ፡ ማመልከት ፡ ስለ ፡ ሕሊና ፡ ጉዳት [22] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የገቡትን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማዶች ፡ ያሟላል ፡፡ ይህም ፡ በቁ ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ "የደም ፡ ዋጋ ፡" ተብሎ ፡ ቀድሞ ፡ በቀላል ፡ አነጋገር ፡ ይጠራ ፡ የነበረውን ፡ ይጨምራል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ በአሁን ፡ ዘመን ፡ ይገኝበታል ፡፡ ይኸውም ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ቀድሞ ፡ የወንጀል ፡ ክስን ፡ ሲያስቀር ፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ ግድን ፡ አያስቀርም ፡ ነበር ፡፡

22. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ ፫ሺ፫፻፵፩—፲፩ ፡፡

(፫ኛ) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መድፈን ፡ ( መሙላት ) ።

ከላይ ፡ ያብራራነው ፡ የመሻሪያ ፡ ሕጉግ ፡ "በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡" የነበሩት ፡ የበፊት ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ ይሽራል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በልማድ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ላልተመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ያገለግላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ሕጎችን ፡ እንኳን ፡ ለማሟላት ፡ አይጠቅምም ። ለማሟላት ፡ ወይም ፡ ለመተካት ፡ የሚጠቅም ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አጋጊው ፡ በጠቅላላ ፡ አብረው ፡ የሚሔዱትን ፡ ሕጎች ፡ በሞላ ፡ በመሻር ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ በሻረ ፡ ነበር ።

ከላይ እንደተመለከተው ፤ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ ፡ ላልተጠቀሱ ፡ ጉዳዮች ፡ በልማድ ፡ በሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ ( የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ የማይቃወሙ ፡ ሲሆን ፡ ) መገልገል ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ ቁጥሮች ፡ ያልሸፈኑዋቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። በበኩሌ ፡ ያገኘሁት ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፤ ይኸውም ፡ በአጋጊው ፡ ከተተወት ፡ ጉዳዮች ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ገንዘብን ፡ በማኅበር ፡ ለማስቀመጥ ፡ ስለሚቋቋሙ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ ከሚናገረው ፡ በቀር ፡ ስለመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይጠቅስም ። መረዳጃ ፡ ማኅበሮችን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፩፻፭ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ሲያደርጋቸው ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፲፪ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይወጣሉ ፡ በተባሉት ፡ አሁን ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ያደርጋቸዋል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ በመስማማት ፡ ብቻ ፡ በልማድ ፡ የሚቋቋሙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፤ ለመበደር ፡ እንዲሁም ፡ ለሌላም ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያገለግሉ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ ዕቁብ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። አብዛኞቹ ፡ ደንቦች ፡ ከጉራጌ ፡ ጎሳ ፡ የመነጩ ፡ ሲሆን ፤ የአሠራራቸውን ፡ ሁኔታ ፡ መግለጽ ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ውጪ ፡ ነው ።[23] ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ሺ፭፻፲፫ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሰው ፡ ባሉ ፡ ልማዶች ፡ የመገልገል ፡ ዕንስ ፡ ሐሳብ ፡ ሌላ ፤ የዕቁብ ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተወሰኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሚያሟሉ ፡ እራሳቸውን ፡ እንደቻሉ ፡ በቀጥታ ፡ ሊገለገልባቸው ፡ ይቻላል ።

23. ስለዚህ ፡ እርእስት ፡ በአዲስ ፡ አበባው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ጥናት ፡ (የኢትኖሎጂ) ፤ ቁ/፰ ፤ ( እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም ) ገጽ ፡ ፹፫ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ "ዕቁብ" ፡ አበሩ ፡ ዳምጤ ፡ የደረሰውን ፡ ተመልከት ።

(፬ኛ) ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ የአህጉራዊ ፡ አውሮፓ ፡ ሕጎች ፡ ዓይነት ፡ ናቸው ። በአህጉራዊ ፡ አውሮጳ ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፤ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ሕግ ፡ መነሻ ፡ ንቅዕ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ዳኛ ፡ ሠራሽ ፡ ስለአልሆነ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕግ ፡ የተያያዘ ፡ እንጂ ፡ የተለያየ ፡ እንዳይሆን ፡ ማድረግ ፡ ተግባራቸው ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ የነሱ ፡ ፍርድ ፡ የማግባባት ፡ ኃይሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ፐላኒዮል ፡ እንደ ፡ ገለጸው [24] "በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ኢ. ኤ. አ. ፲፰፻፺ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ (በፈረንሳይ ፡ አገር ፡) የተቋቋሙት ፡ ሕጎች ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የአህጉራዊው ፡ አውሮጳ ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ጸሐፊች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጣቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸው ። ልማዳዊ ፡ ሕግም ፡ (ከመን ፡ ሎው ፡) ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ይበልጡን ፡ የተመሠረተው ፡ በፍርዳዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ። እንደኋለኞቹ ፡ ያሉ ፡ ሕጎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አከራካሪ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ባጋጠማቸው ፡ ጊዜ ፣ ጉዳዩን ፡ ለመወሰን ፡ ሲሉ ፡ ያወጧቸው ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለማስገባት ፣ ስለማመልከትና ፡ የፍትሐ ፡ ብብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ ስለመድፈን ፡ (ስለመምላት ፡) ከአብራራን ፡ በኋላ ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤን ፡ ልማድን ፡ የምንጠብቅበት ፡ አራተኛ ፡ መንገድ ፡ አድርገን ፡ እናቀርባለን ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ የሰጡትን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ስናስታውስ ፡ ይህ ፡ ፬ኛው ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይይዛል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት [25] ፡ መሠረት ፡ ከበላይ ፡ ሕግ ፡ አውጪዎች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የተናገሯቸው ፡ ቃላት ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ዋጋ ፡ ይኖረዋል ። መሪ ፡ ቃሉም ፡ እላይ ፡ "ገላጭ ፡ ምክንያቶች ፡" እሚለው ፡ ውስጥ ፡ እንደጠቀስነው ፡ "የተሻሩ ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች ፡" ከሚለው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ በመለየት ፡ ከባህልና ፡ ከልማድ ፡ ለመራቅ ፡ አለመታሰቡን ፡ ያሳያል ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የአጋጊውን ፡ ፍላጐት ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ። በአህጉራዊው ፡ አውሮጳ ፡ አብነት ፡ መሠረትም ፡ ይህ ፡ የአጋጊው ፡ ፍላጐት ፡ በቅርብ ፡ የታገጉን ፡ ሕጎች ፡ በምንተረጉምበት ፡ ጊዜ ፡ መሪያችን ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

ከባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ለመራቅ ፡ ያልታሰበ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተገቢው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንጋገር ፡ ልማዳዊ ፡ ትርጉምን ፡ መስጠት ፡ ይኖርባቸዋል ።

24. እላይ ፡ የጠቀስነው ፤ ፐላኒዮልና ፡ ሪፐርት ፡ በቁ. ፲፩ ፡ (ለ) ውስጥ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ፩ ።

25. ለምሳሌ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም.) ቁ. ፹፰ ፡ ጋር ፡ አነጻጸ ፡

ይህን ፥ በሚያደርጉበት ፣ ጊዜ ፣ በጥንቃቄ ፣ መሥራት ፣ አለባቸው ። የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፲፯፻፴፫ ፣ ውሎች ፣ ከዚህም ፣ በላይ ፣ ሕጉ ጎች ፣ ግልጽ ፣ የሆኑ ፣ እንደሆነ ፣ እንዲተረጐሙ ፣ አይፈቀደም ። አብዛኞቹ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥሮችም ፣ ግልጽ ፣ ናቸው ። ዳግም ፣ በቀላሉ ፣ ትርጉ ማቸውን ፣ ከአረፍተ ፣ ነገሩ ፣ ወይም ፣ ከዋናው ፣ በፈረንሳይ ፣ ከተጻፈው ፣ የመ ጀመሪያው ፣ የሕግ ፣ ረቂቅ ፣ መረዳት ፣ ይቻላል ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ግልጽ ፣ ባለ መሆናቸው ፣ ወይም ፣ በጠቅላላው ፣ በመናገራቸው ፣ ከአንድ ፣ በላይ ፣ ትርጉም ፣ የሚሰጡት ፣ የሕግ ፣ ቁጥሮችን ፣ መለየት ፣ ያስፈልጋል ። ልማዳዊ ፣ ትርጉሞ ችም ፣ (፩) የበፊት ፣ ልማድን ፣ ፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ለሚያስገቡ ፣ ወይም ፣ ለሚያመለክቱ ፣ የሕግ ፣ ቁጥሮች ፣ ( ለምሳሌ ፣ የቤተ ፣ ዘመድ ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ) (፪) ከውጭ ፣ አገር ፣ "ለወረስናቸው ፣ ( ለተቀበልናቸው ፣ ) " መሆና ቸውን ፣ ለሚያመለክቱ ፣ የሕግ ፣ ቁጥሮች ፣ በማመዛዘንና ፣ በመጠንቀቅ ፣ ሊሰጡ ፣ ይገባል ። ይኸም ፣ ሲሆን ፣ በተቀበልናቸው ፣ አንቀጾች ፣ ላይ ፣ ያለማመዛዘንና ፣ ያልጥንቃቄ ፣ ልማዳዊ ፣ ትርጉሞች ፣ ሊሰጡ ፣ አይገባም ። ይኸም ፣ የተባለበት ፣ እነዚህ ፣ የተወረሱ ፣ አንቀጾች ፣ ፈልቀው ፣ በተገኙበት ፣ አብነት ፣ ( ዶክትሪን ፣ ) መሠረት ፣ ካልተተረጐሙ ፣ በቀር ፣ ፍች ፣ የማይሰጡ ፣ ከመሆናቸውም ፣ በላይ ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ የተያያዙ ፣ አይሆኑም ። ( ስለተወረሱ ፣ የሕግ ፣ ቁጥሮች ፣ ምሳሌ ፣ ስለግዴታ ፣ ሕግ ፣ እሚለውን ፣ ተመልከት ። ) እነዚህም ፣ የሕግ ፣ ቁጥ ሮች ፣ "በዓለም ፣ ላይ ፣ ከሁሉ ፣ ተሻለው ፣ የሚገኙ ፣ ሕጎች ፣ " እላይ ፣ የተጠቀሰው ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ መቅድም ፣ ) ውስጥ ፣ የተዋስናቸው ፣ ስለሆነ ፣ እዚህ ፣ ሊሰጡ ፣ የተፈለገው ፣ ትርጉም ፣ እዝያ ፣ እንደተሰጡት ፣ ያለውን ፣ ነው ፣

አሁን ፣ ከላይ ፣ ለአቀረብነው ፣ ሐሳብ ፣ ምሳሌ ፣ እንሰጣለን —

(፩) (ሀ) በዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ውስጥ ፣ ልማድን ፣ ማመልከት ፣ በሚለው ፣ ሥር ፣ የቁ. ፲፯፻፰፰ ፣ የመሬት ፣ ሥሪት ፣ የይርጋ ፣ ሕግ ፣ ተወላጆች ፣ የሚከፋፍሉትን ፣ ልማዳዊውን ፣ የጋራ ፣ የመሬት ፣ ርስት ፣ የማይጨምርና ፣ ተወላጅ ፣ የሆነም ፣ ሰው ፣ የትውልድ ፣ ሐረጉን ፣ መዝዞ ፣ ርስቱን ፣ ሊጠይቅ ፣ እንደሚችል ፣ ጠቅሰን ፣ ነበር ። "ተወላጅ ፣ " የሚለውም ፣ አነጋገር ፣ አለመግለጫ ፣ የተነገረ ፣ እንደሆነ ፣ በአውሮጳ ፣ የሚገኘው ፣ አንድ ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ ተብሎ ፣ ይተረጐማል ፣ ( ማለት ፣ አባት ፣ እናትና ፣ ልጆች ፣ ብቻ ፣ ) ። በዚህ ፣ በተጠቀስነው ፣ ቁጥር ፣ ግን ፣ ተወላጅ ፣ ማለቱ ፣ የትውልድ ፣ ሐረጋቸው ፣ የረዘመ ፣ ምንም ፣ ሩቅ ፣ ቢሆን ፣ ርስ ቱን ፣ ሳይከፋፈሉ ፣ ከወረሰው ፣ ከአንድ ፣ የትውልድ ፣ ግንድ ፣ የተገኙን ፣ ተወላ ጆች ፣ (ዘመድ ፣ አዝማድን ፣) ነው ። በዚህም ፣ መሠረት ፣ ተወላጅ ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ በጋራ ፣ ከተያዘው ፣ መሬት ፣ ርስቱን ፣ ለመጠየቅ ፣ ወይም ፣ ድርሻውን ፣ ስጡኝ ፣ ለማለት ፣ በማንኛውም ፣ ጊዜ ፣ ይችላል ። ይኸም ፣ ድርሻን ፣ ለማስጠየቅ ፣ የሚችል ፣ ተወላጅነት ፣ ( የትውልድ ፣ ሐረግ ፣ በቁ. ፭፻፶፩ ፣ (፪) የተወሰነ ፣ ይመ

ስላል ። ይህ ፡ ቁጥር ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ርስቱን ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችለው ፡ (የመሬት ፡ ሥሪት ፡ የደርጋ ፡ ሕጉን ፡ ሊቃወም ፡ የሚችለው ፡) ተወላጅ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ርስቱን ፡ ሳያከፋፍል ፡ ከሞተው ፡ ሰው ፡ ከሰባት ፡ ትውልድ ፡ በላይ ፡ መራቅ ፡ የለበትም ።

(ለ) "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖር ፡" (ቁ. ፯፻፷ ፡) ተብሎ፡ የሚጠራው ፡ እንደጋብቻ ፡ የሚለጥቁትን ፡ ሁለት ፡ ውጤቶች፡ ያስከትላል ። እነዚህም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጊዜ ፡ ስለተጸነሱ ፡ ወይም ፡ ስለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ ማን ፡ መሆን ፡ መገመትና ፡ (ቁ. ፯፻፲፩ ፡ እና ፡ ፯፻፵፰ ፡) ሴትየዋ ፡ ለምትገባባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ የወንድዬው ፡ ዋስትና ፡ (ቁ. ፯፻፲፬ ፤ ከዚህም ፡ ጋር ፡ ቁ. ፯፻፳ን ፡ አነፃጽር ፡) ናቸው ። በቁ. ፯፻፱ ፡(፩) መሠረት ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ግንኙነት ፡ የሚመጣው ፡ የሰውዬውና ፡ የሴቲየይቱ ሁኔታ ፡ "እንደተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ዐይነት ፡" የሆነ ፡ እንደሁ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ማመሳሰል ፡ ልክ ፡ እንደ ሚስት ፡ ሆና ፡(ከቁ. ፰፻፹ ፡ አስተያይ ፡) በደሞዝ ፡ ለምትቀጠረው ፡ ሴት ፡ ይሠራ ፡ አይሠራ ፡ የሆን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ያስከትላል ። ይህ ፡ ማመሳሰል ፡ በደሞዝ ፡ ለምትተዳደረዋ ፡ (እንደ ፡ አሽከር / ገረድ ፡ በደሞዝ ፡ ተቀጥራ ፡ እንደ ሚስት ፡ በሰማንያ ፡ ለምታገለግለው ፡) ይሠራል ፡ ማለት ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ትክክለኛም ፡ ባይሆን ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ አጥጋቢ ፡ መልስ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በደሞዝ ፡ ለሚተዳደሩ ፡ የጭን ፡ ገረዶች ፡ የተወሰነ ፡ መታወቅ ፡ ከመስጠቱ ፡ የተነሳ ፡ የሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ የቀጣሪው ፡ ልጆች ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ይሆናል ።

(፪) (ሀ) በሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ መንገድ ፡ (አርቲፊሴል ፡ ኤንሲሚኔሽን ፡) የሚደረገው ፡ የልጅ ፡ ማስጸነስ ፡ ዘዴ ፡ (ቁ ፯፻፺፬) በኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ ያልታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ጥበባዊ ፡ መንገድ ፡ የተጸነሰን ፡ ልጅ ፡ ስለመካድ ፡ የተደነገገውን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ትርጉም ፡ ዘዴው ፡ ከመነጨበት ፡ አገር ፡ መወሰድ ፡ አለበት ።

(ለ) ከሌላ ፡ አህጉር ፡ የተወረሰው ፡ አብዛኛው ፡ የውል ፡ ሕግ ፡ ሐሳበ ረቂቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፤ ከመነጨበት ፡ አገር ፡ በሮማውያን ፡ አብነት ፡ ትምህርት ፡ ካልተገለጸ ፡ በስተቀር ፡ እምብዛም ፡ ፍችን ፡ አይሰጥም ።

(ሐ) ሆኖም ፤ ውሉ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በውጭ ፡ አገሩ ፡ አብነታዊ ፡ ትምህርት፡ መጠቀም፡ አያሻም ። ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ቁ. ፲፯፻፹፱ ፡ ስለውሉ ፡ አቀራረብና ፡ አቀባበል ፡ በሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ "ፈቃድን - በተለመዱ ፡ ጠቅላላ ፡ ምልክቶች - - - ለማስታወቅ ፡ ይቻላል ፤" ሲል ፡ በልማድ ፡ የሚሠራባ

ቸውን ፡ እንደመጨባበጥ ፡ መሻከት ፡ ፍንጥር ፡ የመሳሰሉትን ፡ ማለቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ የተነጋገርንበትን ፡ ልማድን ፡ ማመልከትን፡ እንዴን ፡ ሁኔታ ፡ ያሳያል ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያቀረብናቸውን፡ ሐሳቦች ፡ ቢቀበሉም ፡ ባይቀበሉም ፡ ተፈላጊው ፡ ነገር ፡ ትርጉም ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሁልጊዜ ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ትርጉም ፡ መድናታቸው ፡ እንዲያገ ፡ ነው ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርዳዊ ፡ ሕግ ፡ በማበጀት ፡ ፈንታ ፡ ሕግ ፡ የለሽነትን ፡ ያስገኛሉ ። በዚህ መጽሔት ፡ የሚታተሙትም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮችና ፡ ቃላቶች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ፍች ፡ እንዲኖራቸውና ፡ የተያያዙ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳሉ ። ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ፍች ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቦች፣ በዚሁ ፡ መጽሔት፡ በአንደኛ ፡ ፸ልዩም ፡ (፲፱፻፶፪) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፱ ፡ ላይ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፤ ከጂ. ክሽቾኖቢች ፡ "ዐዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ትርጉም፡ (ፍች) ፡ በኢትዮጵያ ፡ " በሚለው ፡ አርእስት ፡ ጽፎ ፡ የገለጸውን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

(፫ኛ) በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ።

ከላይ ፡ የተነጋገርንባቸው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ በልማድ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚያገለግሉ ፡ መንገዶች ፡— ልማድን ፡ በሕግ፡ ማስገባት ፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ (መጥቀስ) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መምላትና ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ፡ ያሉት ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ችግር ፡ በሙሉ ፡ አያጠናቅቁም ። ስለዚህ ፡ ሽሪው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ በመኖሩ ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ሕጋዊነት ፡ የሌላቸውን ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ የሚገለግሉባቸውን ፤ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶችን፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ፡ ነው ።[26] እነዚህም፡ (፩ኛ) ፡ ስለቤተዘመድ ፡ የተጻፉት ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ለባልና ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ለሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ የሚተውት ፡ ሕጎች ፤ (፪ኛ) የግል ፡ ውል ፡ በተዘዋዋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦችን ፡ የሚፈቅድባቸው ፡ ሕጎች ፤ ስለማኅበር ፡ በወጡት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ መንገዶች ፡ ናቸው ።

(፩ኛ) ስለቤተዘመድ ፡ ሕግ ።

ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነው ፡ የቤተዘመድ ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ትጽዕኖ ፡ የሀገርን ፡ ወግ ፡ በማመልከት ፡ (በመጥቀስ) ፡ ተቃ

26. በልማድ ፡ ሕግ ፡ ለመጠቀም ፡ ዋና ፡ ፍንጭ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አርእስት ፡ ሥር ፡ ለመተንተን ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆነው ፡ ምናልባት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጋችን ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ አለመኖሩ ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፩፻፳፭ ፡ የተከለከለው ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ እንኳ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። (ቁ- ፮፻፲፱) ። የመጀመሪያው፡ (በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ ፮፻፲፭፡ መሠረት ቅጣት ፡ ስለሚደርስበት ፡ ) ይህንን ፡ ለማድረግ ፡ አይደፍርም ። ሁለተኛው ፡ ማለት ፡ ዐቃቤ፡ሕጉም የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ ተግባር ፡ በግዴለሽነት ፡ ያልፈዋል ። ይህም ፡ ታላቅ ፡ ፍንጭ ፡ የልማድ ፡ ሕግን ፡ በመጠበቅ ፡ ረገድ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ከማብራራት ፡ ይልቅ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ ጥናት ፡ ይጠይቃል ።

ልሏል ፣ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣወን ፤ በጋብቻ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚያጸድቁ ፡ ሕጉ ፡ ሳይረሰው ፣ ትጽዕና ፡ ትራስ ፡ የሚሆኑለትን ፡ ሁለት ፡ ብልሃቶችን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እንመረምራለን ።

(ሀ) የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሊሰፋና ፡ ሊጠብ ፡ በሚችል ፡ አዛኘር ፡ በሆነ ፡ መብት ፡ ሰጭ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ ለልማዳዊ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ (የጋብቻ ምስክሮች) ፡ ሰፋ ፡ ያለና ፡ ያልተወሰነ [27] ፡ ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣቸዋል ። ይህም ፡ ሥልጣን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚነሱት ፡ ጠቦችና [28] ፡ ስለጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ እንዲሁም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በሰዎችና ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጡ ፡ ያስችላቸዋል ። [29] ውሳኔአቸውም ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ ውጭ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ማጓደላቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይግባኝ ፡ አይባልበትም ፡ (ቁ-፯፻፴፯) ። የመተጫጨት ፡ ሥርዐት ፡ ምስክሮችም ፡ በመተጫጨት ፡ ጉዳይ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ሲነሳ ፡ ይዳኛሉ ፡ (ቁ. ፯፻፳፫) ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ኻሪው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብ.ሔር ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ሁኔታ ፡ ባለማመልከቱ ፡ "የተሻሩት ፡ "የአገር ፡ ልማዶች ፡ በመሠረቱም ፡ ባይሆን ፡ በሁናቴው ፡ አኳኋን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲውሉ ፡ (እንዲገቡ) ፡ በር ፡ ይከፈትላቸዋል ። ስለ ፡ ዚህ ፡ የተሻሩት ፡ የልማድ ፡ ሕጎች ፡ በማይቀረው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አማካኝነት ፡ እንደገና ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

(ለ) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ-፯፻፳፯ ፡ እና ፡ ፯፻፴፪ - ፴፫ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ልምድ ፡ ሌሎችን ፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ መንገዶች ፡ ይሰጣሉ ። እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ አግቢው ፡ ወይም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ባንድነት ፡ (ከጋብቻ ፡ በፊት) ፡ ወይም ፡ በቤተዘመድ ፡ ሽማግሌች ፡ በኩል ፡ (በጋብቻ ፡ ጊዜ) በመካከላቸው ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ያለበትን ፡ ግዴቴዎችና ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ውጤት ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ይፈቅድላቸዋል ። (በዚህ ፡ ረገድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ በስተቀር ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እንዳሻቸው ፡ እንዲዋዋሉ ፡ ይፈቅዳል ። ከዚህ ፡ አቀራረብ ፡ ጋር

27. ለምሳሌ ፤ ከቁ ፡ ፯፻፶፩ ፡ (፪) ፡ ጋር ፡ አነፃጽር ።

28. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ/፯፻፵፩ ፡ (፪) ፡ ፯፻፵፰ ፡ (፩) ፡ ፯፻፶፩ ፡ (፩) ፯፻፶፪ ፡ (፫) ፯፻፷ ፡ (ሐ) እንዲያውም ፡ ዋናውን ፡ ስለ ፡ ነገር ፡ አባት ፡ የሚመለከተውን ፡ (ቁ/፯፻፶፩) ፡ ተመልከት ። ይህም ፡ የነገር ፡ አባት ፡ የጋብቻ ፡ አስታራቂ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፤ ከምስክሮቹ ፡ ውስጥም ፡ "የመጀመሪያው ፡ ምስክር " ፡ እና ፡ ወይም ፡ ለጋብቻ ፡ ሁናቴ ፡ ዋስ ፡ የሚሆነው ፡ እሱ ፡ ነው ።

29. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ.፯፻፳፯—፴፯ ፡ ፯፻፶፩—፶፩ ፡ እንዲያውም ፡ ዋናውን ፡ ቁ. ፯፻፳፯—፳፰ ፡ ተመልከት ።

ቁ. ፲፻፴፬ን ፡ እንጸጽር ።) በራሳቸው ፡ ብቻቸውን ፡ ሕጋዊ ፡ ያልሆኑ ፡ ልማዶች ፡ በጋብቻ ፡ ስምምነት ፡ ወ ስጥ ፡ ሰግረው ፡ እንደሚገኙ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ሆኖም ፡ በትእዛዛዊ ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ የተወሰነውን ፡ የመረዳዳትና ፡ የአብሮ ፡ መኖር[30] ፡ ግዳጅ ፡ ማክበር ፡ አለባቸወ ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ አንዱ ፡ ወ ጤት ፡ ዓለም በሞላ ፡ የግል ፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች ፡ የማይለውጡ ፡ የማይሸጡ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ከሚያምንበት ፡ መሠረት ፡ ሐሳብ ፡ በመለየት ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በመካከላቸው ፡ ስላ ለው ፡ ግንኙነትና ፡ የግል፡ መብታቸውንና ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ያለውን ፡ ግዳጅ ፡ በራ ሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ እንዳሻቸው ፡ መወሰን ፡ እንዲችሉ ፡ አድርጓቸዋል ፡ (ቁ· ፲፻፳፯ (፪) ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እነዚህን ፡ መብትና ፡ ግዳጆች ፡ ሊያሻሽሉ ፡ ይችላሉ ፡ (ቁ. ፲፻፴፪ (፪) ) ። የዚህም ፡ ዐይነት ፡ የጋብቻ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ መሻሻል ፡ ትእዛዛዊ ፡ ሳልሆን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ተቃራኒ ፡ ሆኖ ፡ ለምሳሌ ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራው ፡ በሚስቲቱ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በባልየው ፡ ነው ፡ (ከቁ. ፲፻፵፯ ጋር ፡ አነፃጽር) (በጣም ፡ የራቀ ፡ ምሳሌ ፡ ቢሆንም) ፤ ወይም ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታቸውን ፡ የምትመርጠው ፡ ሚስቲቱ ፡ ነች ፡ (ከቁ-፲፻፵፩ ፡ ጋር ፡ አነ ፃጽር ) ፤ ማለት ፡ ይችላል ። ጠልቆ ፡ ላልተመራመረ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ስምምነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፵፫[31] ፡ የተወሰነውን ፡ የመተማመን ፡ ግዴታ ፡ ሕግ ፡ ሊሽረው ፡ ወይም ፡ በአንዳንድ ፡ የአገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ግዳጅ ፡ በሚ ስቲቱ ፡ ላይ[32] ፡ ብቻ ፡ ሊወስነው ፡ የሚችል ፡ ይመስለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወን ጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (ቁ. ፲፻፲፭) ዝሙትን ፡ ስለሚከለክል ፤ ይኸን ፡ ለማድረግ ፡ አይ ቻልም ።

ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጋብቻ ፡ ለተጋቢዎቹ ፡ መብትና ፡ ግዳጃቸውን ፡ በራሳ ቸው ፡ (ምናልባት ፡ የልማድን ፡ ሕግ ፡ በመከተል) ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ የሚ ሰጥ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ አስተያየት ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ። ዳግም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የማያጋጥመው ፡ በጋብቻ ፡ ላይ፡ የሚነሳ፡ ጸብ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያገኘው፡ "በልማድ" ፡ በተመሠረተው፡ የሽምግልና፡ ዳኝነት ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሆኖ ፡ ልማድን ፡ ከአንድ፡ ሕጋዊ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ ሳያያይዙ ፡ "እንዲያው ፡ ጥሬውን ፡ በቀጥታ ፡ " ማመልከት ፡ (መጥቀስ) የተከለከለ ፡ ነው ። (ቁ· ፲፻፴፩)

(፪ኛ) <u>ግልግል (ስምምነት)</u> ።

የቤተዘመድ ፡ ሽማግሎችን ፡ (የጋብቻ ፡ ምስክሮችን ፡) ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ አብራርተን ፡ ሰጥተናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚሀ ፡ ውጭ ፡ በግዴታ ፡ ወይም በፍ

30. ቁ ፮፴፮ እና ፲፻፵ን እንዲሁም ትእዛዛዊ ቁጥር የሆኑትን ፲፻፷፰—፹፬ ።

31. የተለየ ፡ ስምምነትን ፡ ማድረግን ፡ የሚከለክለውን ፡ ንዑስ ፡ ቁ/(፫) ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ከሚሊየን ሥርዞታል ። የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ <u>ግረሚያ</u> ፡ ተመልከት ።

32. ይህም ፡ ዝሙትን ፡ ለጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በቁ. ፲፻፳፰—፳፱ ፡ መሠረት ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ከመሆን ፡ አያስቀረውም ።

ትሕ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ በወል ፡ ባልሆነው ፡ በልማድ ፡ በአዛወንቶች [33] ፡ የሚደረገው ፡ ዕርቅ ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ሊነካ ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ የመስማማቱ ፡ ግዴታ ፡ ይጫናቸውና ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ስለማይፈቅዱ ፡ ጉዳዩ ፡ በዕርቅ ፡ ስለሚያልቅ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፤ በውርስ ፡ መሻል ፡ የሚነሳ ፡ አለመግባባት ፡ በፍትሐ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሻረ ፡ ቁጥር ፡ በተሻረው ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ ውሳኔ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ። የሚያገኘው ፡ ውጤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ስለግልግል [34] ፡ በሚፈቅደው ፡ ውል ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ ያሉ ፡ ግልግሎች ፡ በፍትሐ ብሔር ፡ ቁ. ፫ሺ፫፻፲፪ ፡ የተደነገገው ፡ "የመብት ፡ ስሕተት ፡" የማይለውጣቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ናቸው ። ይኸም ፡ ማለት ፡—

(፩) ግልግል ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ይግባኝ ፡ ሳይገረው ፡ መጨረሻ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተፈረደ ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፪) ግልግል ፡ ያደረጉበትን ፡ መብቶች ፡ በመመልከት ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ በተደረገው ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ግልግል ፡ ሊነካ ፡ አይቻልም ።

ከዚሁም ፡ የተነሳ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ (ለምሳሌ ፡ የውርስ ፡ መብት ፡) ባለማወቅ ፡ ስምምነት ፡ (ግልግል) ቢያደርግ ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ ስምምነት ፡ አይሻርም ። ስለዚህ ፡ በሕግ ፡ የተሻረው ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ ይገኛሉ ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በመሆናቸው ፡ ሳይሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ግልግል ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። እንደዚሁ ፡ ያሉ ፡ ባህላዊ ፡ ሕጎች ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ ለሚያጠኑ ፡ ሊቃውንት ፡ እንጂ ፡ ለሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ጥናት ፡ አይስማሙም ፡ ይህም ፡ አለመስማማት ፡ ለግልግል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጋብቻም ፡ በኩል ፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የምንጠቀምባቸው ፡ ልማዶች ፡ ጥምር ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ልማዶች ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ በግልግል ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ቢገኙ ፡ እንጂ ፡ ለብቻቸው ፡ እራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ዋጋ ፡ አይኖራቸውም ።

(፫ኛ) ማኅበሮች ።

ባህላዊ ፡ የሆኑ ፡ በዕድሜ ፡ በዝምድና ፡ በሃይማኖት ፡ (ቁ-፬፻፯) ተመሥርተው "ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡" እንዳልተቋቋሙ ፡ (ቁ. ፬፻፬) ሕጋዊ ፡ ማኅበሮችን ፡ ለማወቅ ፡ (ለመቀበል ፡) ይቻላል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማኅበ ፡

33. ሽማግሌ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ።

34. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ/፫ሺ፫፻፭—፰ ።

ሮቹ ፡ ደንብ ፡ አሠራነት ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ሕጋዊ ፡ የማኅ
በር ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው (ቁ· ፬፻፰) ። ነገር ፡ ግን ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ሲታይ፡
ለእንደዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ ጉዳይ ፡ መወያየትም ፡ የሚያሻ ፡ አይመስልም ፤ ምክንያ
ቱም ፡ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የተመሠረቱ ፡ ጉባዊ ፡ ክፍሎች ፡
ወይም ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ የተነሣ ፡ ጭቅጭቅ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ፍርድ፡ ቤት፡
ተወስዶ ፡ መወሰን ፡ ስለማያሻው ፡ ወይም ፡ እንዳያውም ፡ ስለማይፈለግ ፡ ነው ።
(የዶርዜዎችን ፡ ማኅበር ፡ የጉራጌዎችን ፡ ማኅበር ፡ የመሰለውን ፡ ማለታችን ፡
ነው ። )

## መደምደሚያ ።

ልማድን ፡ የሚሽረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ልማድ ፡ ኢትዮጵያ
ውስጥ ፡ ሕግን ፡ ተመርኩዞ ፡ እጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ክፉኛ ፡ ይወስነዋል ።
ይህ ፡ መወሰን ፡ የአገሪቱዋ፡ ልዩ፡ ባህልና ፡ ሁኔታ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገው ፡ ሲሆን ፤
በኃይል ፡ ወደ ፡ ማስተባበር ፡ (አንድ ፡ ወደ ፡ ማድረግ ፡ ) ዝንባሌ ፡ አደረሰ ። ይኸም
ሆኖ ፡ ከላይ ፡ ከተብራራው ፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ ከሆኑ ፡ ልማድን ፡ መጠቀሚያ ፡
መንገድ ፡ ሌላ ፡ ጠልቆ ፡ መመርመር ፡ ልማድን ፡ የምንጠቀምባቸው ፡ አራት ፡
ሕጋዊ ፡ መንገዶች ፡ እንዳሉ ፡ ገልጸልናል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ልማ
ድን ፡ የማስገባቱ ፡ መንገድ ፡ ተጨማሪ ፡ አዲስ ፡ ልማዶች ፡ እንዳይገቡ ፡ በማገድ ፡
ተዘግቷል ፡ (ቁሟል) ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ አዲስ ፡ ልማዶች ፡ ለማስገባት ፡ ልንጠቀ
ምበት ፡ አንችልም ። የቀሩት ፡ ሦስቱ ፡ መንገዶች ፡ ግን ፡ ማለት ፡ በሕግ ፡ ልማ
ድን ፡ ማመልከት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ስፍራዎችን ፡ መሙላትና ፡ ፍር
ዳዊ ፡ ዘይቤ ፡ እንደ ፡ ቅሉም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ጥናት ፡ እንዲኖር
አድርገዋል ። በሕግ ፡ በኩል ፡ ዋጋ ፡ ቢኖራቸውም ፡ ባይኖራቸውም ፡ የሰውን -
ዘር ፡ሁኔታ ፡ ለሚያጠኑ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የጥናቱ ፡ አነስተኛ ፡ መጠን ፡ የለውም ።
በሰፊው ፡ ማጥናት ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ የሆነ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡
ጥናቱና ፡ መመራመሩ ፡ መንግሥት ፡ ባጸደቀው ፡ ልክ ፡ (መጠን) ፡ መወሰን ፡ ይኖ
ርበታል ። በተጨማሪ ፡ ሲያስፈልግ ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የዘር ፡ እጥኚውን ፡
የዕውቀት ፡ ድርድር ፡ በሕግ ፡ አስተያየት ፡ መምከር ፡ ቢችል ፡ ትክክለኛው ፡ የጥ
ናትና ፡ የምርምሩ ፡ መነሻ ፡ ነቅዕ ፡ ልማድ ፡ እንዲሠለጥን ፡ (እንዲገዛ) ፡ የተረጋገ
ጡበት ፡ ወይም ፡ ማስታወሻ ፡ የተወሰዱባቸው ፡ ወይም ፡ ልማዳዊ ፡ አተረጓጐም፡
የጸኑባቸው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መግለጫዎች ፡ ናቸው ። የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ
ብሔር ፡ ሕግ ፡ አዲስ ፡ ስለሆነና ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮች ፡ መታ
ተም ፡ ስላልተስፋፋ ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ያብራራነውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚዘረዝሩ ፡
የታተሙ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የሉም ። ስለዚህም ፡ በፍርድ ፡ ቤት
የተወሰኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ መግለጫ ፡ ተመርኩዞ ፡ የሕግ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ ሰማ

ድረግ ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ ጥቂት ፡ ነው ። ክርክሬም ፡ የማይዳሰስ ፡ (የማይጨበጥ) ፡ ጠባይ ፡ የኖረው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲያደረግልኝ ፡ እለምናለሁ ።

የአገር ፡ ልማድ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ በሆነበት ፡ ቦታ ፡ የቤት ፡ ዘመድን ፡ የርስትንና ፡ የውርስን ፡ ጉዳዮች ፡ ጨምሮ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማዘጋጀቱ ፡ በገቢር ፡ አይቻልም ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ በብዙ ፡ የታወቁ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት 35 ፡ ተገልጸዋል ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ በአፍሪቃ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልተደረገ ፡ ሲሆን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ከላይ ፡ በዘረዘርናቸው ፡ ስምሙ ፡ ብልሃቶች ፡ በመጠቀም ፡ ሊፈጸም ፡ ተችሏል ። ልማድን ፡ በሰፊው ፡ የሚሽረውና ፡ ሁሉን ፡ ጠቅሎ ፡ የሚይዝ ፡ ይህ ፡ አንዳች ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይህን ፡ ወይም ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ፡ ብሎ ፡ አስቀድሞ፡ መተንበይ ፡ አጉል ፡ ግምት ፡ ይሆናል ። አዲስ ፡ ሕጋዊ ፡ ልብስ ፡ ምንም ፡ ተወዳዳሪ ፡ በሌላቸው ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ ልብስ ፡ ሰፊዎች ፡ ቢሰፋም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ አካል ፡ መኰስኰሱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ከላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ የልማድን ፡ መጠቀሚያ ፡ መንገዶች ፡ በተያያዘ ፡ ሁኔታ ፡ በመከተልና ፡ እነሱንም ፡ የሚመለከትን ፡ ውሳኔ ፡ በመግለጽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከአሮጌ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ጉዳና ፡ መሸጋገር ፡ የሚፈጥረውን ፡ ችግርና ፡ አለመረጋጋጥ ፡ ለማቃለል ፡ እንደሚችሉ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። 36

35. ለምሳሌ ፤ እላይ ፡ የጠቀስነው ፡ አቦቴኒ ፡ ገጽ ፡ ፰ ፡ ላይ ፡ የገርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፲፩ ።

36. አሁን ፡ በሚወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚታተመውን ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች» ፡ የተባለውን ፡ የፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደ ጽሑፍ ፤ ጽሑፌ ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ተመልክቼዋለሁ ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ሕግ ፡ ታሪክና ፡ ይህም ታሪክ ፡ ስለሚገኝበት ፡ ጽሑፎች ፡ የተጻፈው ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕጋዊ ፡ ሐተታው ፡ እምብዛም ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። ስለ ፡ ልማድ ፡ በሚናገረው ፡ በክፍል ፡ ሀ) ፩ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለጻፍኩት ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ ጽሑፌን በሰፊው ፡ ስለሚያብራራው ፡ ሐተታ ፡ ሰጥቶዋል ። ይህም ፡ የሰጡት ፡ ሐተታ ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ፡ ነገሮችን ፡ ከመጥቀሱ፡ በላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አተረጓጓም ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነው ። የልማድ ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ስለሚውልበት፡ ሁኔታ ፡ (ስለ ፡ እስላምና ፡ ሕግ ፡ እና ፤ ክፍል ፡ ፩ ፡ ተመልከት) ሊቁ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞችን ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ በጣም፡ የተጋነነ ፡ ነው ። በእኔ ፡ የተመጠነ ፡ አስተያየት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አወጣጥ ፡ መመሪያ ፡ ሐሳብ ፡ (ፖሊሲ) ከተጻፉትም ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ።

ፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ ሕግን ፡ ለማሻሻል ፡ ልማድን፡ ማጥናት ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚለውን፡ ሐሳብ ፡ ለማስፋፋት ፡ የፈለጉ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሙከራ ፡ የተከተልን ፡ እንደሆን የልማድን ፡ ሕግ ፡ ለማጥናት ፡ ሲባል ፡ «የሕግን ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ» ፡ ይሆናል ፤ እንደ ዚሁ ፡ ዓይነቱን ፡ አስተያየት ፡ በአጭሩ ፡ ለማስቀረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥን ቦታ ፡ እንዳገኘሁ ፡ በሰፊው ፡ አብራራለሁ ። ይህም ፡ ማብራሪያ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደንን ፡ መልካም ፡ ሥራዎች ፡ አይጠቅስም ።